ሰላሑዲን አል-አዩቢ

(1137-1193)

Jama'aa muslimaa yuuniversitii jimmaa
ጅማ ቶኒቨርሲቲ ሙስሊም ጅማዓ
Jimma University Muslim Jama'a
جماعة طلاب المسلمين



አዘጋጅ፡- ዐብደላህ ናሲሕ አል-ዐልዋን

ትርጉም፡- አብዱልከሪም ታጁ

አርትኦት፡- ሑሴን ከድር

እና

ሙስጠፋ ሓሚድ

© መብቱ ለነጃሺ ማተሚያ ቤት
በሕግ የተጠበቀ ነው።

የካቲት 2006

የመጽሐፉ ርዕስ
ሰላሐዲን አል-አዩቢ

ትርጉም
አብዱልከሪም ታጁ

አርትዖት
ሁሴን ከድር እና መ·ስጠፋ ሓሚድ

ትየባ እና ጽሑፍ ለቀማ
ሰዓዳ አብዱ

ሽፋን ዲዛይን
ዩሰራ አሕመድ

ሴይአሙት
ሐያት ፍቃዱ

ነጃሺ ማተሚያ ቤት ኃ.የተ.የግ.ማ.
☎ 011-2765027, 011-1577357/90
011-1577391 ✉ 50514
e-mail: nejashi@ethionet.et
nejashi press@gmail.com
አዲስ አበባ

ማውጫ

መግቢያ ..... ፡

ምዕራፍ አንድ 6

የሰላሐዲን ማንነት 6

ምዕራፍ ሁለት 13

የአስተዳደሩ መጀመሪያ 13

ምዕራፍ ሦስት 18

ሰላሐዲን በግብፅ ውስጥ 18

ከኑረዲን ጋር የነበረው የግንኙነት ፖለሲ 24

ምዕራፍ አራት 27

ሰላሐዲን በሶሪያ 27

ሰላሐዲን በደማስቆ 28

ሐምስ፣ ሐማህ እና አሌፖ 31

ምዕራፍ አምስት 36

በአመራሩ ሥር አንድ የሆኑ አገሮች 36

ምዕራፍ ስድስት 41

የመስቀለኞች ሲራና ጦርነት 41

የመስቀል ዘመቻዎች ምን ዓይነት ዘመቻዎች ነበሩ? 41

የመጀመሪያው የመስቀል ዘመቻ እና የእየሩሳሌም መወረር 42

ለመስቀል ወራሪዎች ድል ዋና ዋና ምክንያቶች 44

ሁለተኛው የመስቀል ጦርነት፡- የሐቲኖጢን ድል መግቢያ 45

ምዕራፍ ሰባት 46

በሐቲኖጢን ጦርነት ላይ የሰላሐዲን ድል ማድረግ 46

የጦርነቱ ምክንያቶች 46

የሐቲኖጢን ጦርነት እና የእየሩሳሌም መመለስ 47

ሰላሐዲን የመስቀል ወራሪዎችን የያዘበት ሁኔታ 55

CamScanner

የአከራ መከበብና ሦስተኛው የመስቀል ዘመቻ .....
የጀርመን ዘመቻ .....
የፈረንሳይ እና የእንግሊዝ ሠራዊቶች .....
የሙስሊሞች ተጋድሎ .....
የጦርነቱ ማብቃት .....

ምዕራፍ ስምንት .....
የሰላሐዲን መጨረሻ .....

ምዕራፍ ዘጠኝ .....
የሰላሐዲን ባህሪያት .....
በሰላሐዲን ላይ የተሰነዘረ ትችት .....
የግዛም እና የሥነ-ዕሁፍ ፍቅር .....
ዙህድ (ቀላል ሕይወት መምራት) እና ለጋስነት .....
የጅሃድ ፍላጎት እና እንቅስቃሴ .....

ምዕራፍ አስር .....
በሰላሐዲን የተላከ የተሐድሶ እርምጃዎች .....

ምዕራፍ አስራ አንድ .....
የድሉ አንኳር ምክንያቶች .....

ምዕራፍ አስራ ሁለት .....
ፍልስጤም ከትላንት እስከዛሬ .....

ማጠቃለያ .....

መግቢያ

ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይሁን፣ የአላህ ሰላምና ፀጋ በአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ፣ እንዲሁም በባልደረቦቻቸው እና እስከመጨረሻው ቀን ድረ ፈለጋቸውን በተከተሉ ሰዎች ላይ ሁሉ ይሁን። አሚን!

በታሪክ ውስጥ ስላለፉ ታላላቅ ስብዕናዎቻችን፣ ስለፍትህ የታገሉ መሪዎቻችን እና ስለተሐድሶ ሐዋሪያቶቻችን ሕይወት ማውራት እጅግ በጣም ውድ ወግና መተኪያ የሌለው ትውስታ ነው፤ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች የኡማው መሪ ብርሃኖች ነበሩ። ዑማውን ወደ ትክክለኛው ጐዳና ከመሩ ታላላቅ ሰዎች ውስጥ አንዱ ደግሞ ሳላሃዲን አል-አዩቢ ነበር።

ምናልባት "ደራሲው ከሌሎች ስብዕናዎች ሁሉ በላይ ለምን የሰላሑዲንን የሕይወት ታሪክ መረጠ" ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል። ምላሹም ይኸው ነው፡- የሳላሃዲን ሕይወት ሁሉም ሰው ከሚያውቀው ደማቅ ድል እና እየሩሳሌምን ከመስቀል ወራሪዎች ነፃ ከማውጣት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው። በዚያውም ያሁኑ ትውልድ ሒጥጢን ጦርነት የተገኘውን ድል ሚስጥርን እና ምክንያቶቹን ሊያይበት ይችላል ብዬ ስለገመትኩ፣ እኔንም ኢ-ፍትሐዊ ከሆኑት ዕዮናዊያን እና በምዕራብም ይሁን በምስራቅ ከሚገኙ ረዳቶቻቸው እየሩሳሌም ነፃ ወደምትወጣበት ትክክለኛ መንገድ የሙስሊሙን ዑማ ትኩረት ለመሳብ ይረዳኛል ብዬ ስላሰብኩ ነው።

በዚህ መጽሃፍ ምዕራፎች ውስጥ አንድ አረብ ያልነበረ ኩርዳዊ ግለሰብ፡- እንዴት አድርጐ እንደዚህ ዓይነት ትልቅ ድል ሊያሳካ እንደቻለ፣ ተበጣጥሶ የነበረውን ሙስሊም ዑማ እንዴት በተዋጣለት አመራሩ ሥር ወደ አንድነት እንዳመጣ፣ ሕዝቡ ኢስላማዊውን ሸሪዓ እንዲከተል እንዴት ማሳመን እንደቻለ፣ የአላህን ቃል የበላይ ለማድረግ እንዴት በኢስላም ስም እንደታገለ እና ጠላቶቹን እንዴት በመልካም ባህሪዎች እና ሥነ-ምግባሮች እንደያዛቸው አንባቢያን ይርረዱባቸዋል።እንዲሁም ከሌሎች ተለይቶ ይታወቅባቸው የነበሩ ምርጥ ባህሪዎቹን እና ያሳካቸውን የተሐድሶ ተግባራት ያውቁባቸዋል። ባጭሩ ሰላሑዲን ማን እንደነበር በሚገባ ይመለከቱባቸዋል።

ምዕራፍ አንድ

የሰላሑዲን ማንነት

የዘር ሀረግ

ሰላሑዲን ግብዕንና ታላቋን ሶሪያ (የዛሬዎቹን ሶሪያን፣ ሌባኖስን ፍልስጤምን) ጠቅልሎ ከገዛና ከተከበረ ኩርዳዊ ቤተሰብ ተወለደ። ግዛ የአዩቢድ ግዛት ተብሎ ይጠራ ነበር። የሰላሑዲን የዘር ሃረግ ከትላልቅ የኩርድ ጎሳዎች ውስጥ አንዱ ከሆነው ከ ‹አረወዲያ›[1] ይመዘዛል፡ አንዳንድ የታሪክ ምሁራን ግን የዘር ሃረጉ በሙደር በኩል ከዓድናን ጎ ጋር እንደሚገናኝ ጠቅሰዋል። እነዚህ የታሪክ ምሁራን የእያንዳንዱን ትልቅ ስብዕና የዘር ሀረግ ከአረቦች ጋር የማያያዝ አባዜ እንደተጠናወታቸው አያጠራጥርም። ሌሎች ህዝቦች ባህልና አኩሪ ታሪክ መሥራት የማይችሉ ይመስል መልካም ተግባራትንና የሞራል ድርጊቶችን በሙሉ በአረቦች ዙሪያ ብቻ አጥረው ለማስቀረት የሚያደርጉት ሙከራ ከምርምር መርሆዎችና ከዕውነታ ጋር ይላተማል።

ታላላቅ ስብዕናዎችን በታሪክ ውስጥ ብናስስ ባህልን እና ስልጣኔን በመገንባት በኩል ትልቅ ሚና የነበራቸው ታላላቅ ስብዕናዎች ብዙዎቹ አረብ አለመሆናቸውን እንረዳለን። ስለዚህ የሁሉንም ታላላቅ ስብዕናዎች የዘር ሃረግ በሃሰት መንገድ ከአረቦች ጋር ለማገናኘት የሞከሩ ከላይ የጠቀስናቸው ዓይነት ምሁራን በኢስላም የተወገዙትን የተዛባ አጥባቂነትንና የዘር መድሎን ሲያበረታቱ መኖራቸው ሊታወቅ ይገባል። ቁርአን ይህን አውጇል፡-

﴿ إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ إِخْوَةٌ فَأَصْلِحُوا۟ بَيْنَ أَخَوَيْكُمْ ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ ﴿١٠﴾ ﴾

الحجرات: ١٠

"ምእመናናች ወንደማማቾች ናቸው፤ በሁለት ወንደሞቻችሁም መካከል አስታርቁ፤ ይታዘንላችሁም ዘንደ አላህን ፍሩ።" (አል-ሁጁራት፡ 10)

---

[1] ይህ ጎሳ አዘርባጃን ውስጥ በምትገኝ ገጠራማ መንደር አካባቢ ነበር የኖረው የሰላሑዲን አባት አዩብ ኢብን ሻዚ የተወለዱትም በዚችው መንደር ውስጥ ነበር።

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن ذَكَرٖ وَأُنثَىٰ وَجَعَلۡنَٰكُمۡ شُعُوبٗا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓاْۚ إِنَّ أَكۡرَمَكُمۡ عِندَ ٱللَّهِ أَتۡقَىٰكُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٞ ١٣ ﴾ الحجرات: ١٣

"እላንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፡ እንድትተዋወቁም ገላዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፡ አላህ ዘንድ በላጫችሁ፡ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፡ አላህ ገፅጸን ወዋቂ፡ ውስጥንም ወዋቂ ነው።" (አል-ሑጁራት፡ 13)

ከዚህ ቡኋላ ምን ይፈልጋሉ?

ሰላሑዲን የኩርዳዊው ነጅሙዲን አዩብ ኢብን ሻዚር ኢብን መርዋን ልጅ ነበር።

ልደት፡

ሱልጣን የሱፍ ሰላሑዲን በሒጅራ አቆጣጠር 532 (አ.ኤ.አ 1137) ጥንታዊ ግንቦች በሚገኙባት ጥንታዊ መንደር ውስጥ ተወለደ። ከባግዳድ ከተማ በትርብ ርቀት ላይ የምትገኘው ይህች መንደር ተከራት ተብላ ትጠራ ነበር። ከድሮ ጀምሮ ለፐርሺያ ንጉሶች የጦር መሣሪያ ማከማቻ መጋዘኖች እና የመቆጣጠሪያ ማማዎች በመሆን ሲያገለግሉ የኖሩት ጥንታዊ ግንቦቿ በቲግሪስ ወንዝ ላይ የተገነቡት በቀደምት የፐርሺያ ንጉሶች ነበር። በዑመር ኢብን አል-ኸጣብ ዘመን (በ16 አ.ሒ.) ተክራት በሙስሊሞች ተያዘች።[2]

ተክራት በተለያዩ የሙስሊም መሪዎች ቁጥጥር ስር ሆና ለረጅም ጊዜ ቆየች። ሰልጁቅ ቱርክስ ወደ ስልጣን በመጣ ጊዜ፣ የሰላሑዲን አባት ነጅሙዲን አዩብ ኢብን ሻዚ ባግዳድ ውስጥ የሰልጁቅ ፖሊስ ትልቅ ባለስልጣን ከነበረው ከሙጃሂዱዲን በህሩዝ ጋር ተገናኘ። ባለሥልጣኑ አዩብን የተክራት ተቆጣጣሪ አድርጎ ሾመው። ወንድሙን ሻርክህ አሰዱዲንን ደግሞ ረዳቱ አደረገለት። በዚህ ምክንያት ሁለቱ ወንድማማቾች አዘርባጃን ውስጥ የምትገኘውን ዳዊንን ለቀው ወደ ዓራት ተጓዙ። ሁለቱ ርዳዊ ኩርዶች በበህሩዝ የፖሊስ ተቋም ውስጥ ለመሥራት ወደ ተክራት መጡ።

[2] ሙዕጀም አል-ቡልዳን ቅፅ 2 ገፅ 491

በሚያስገርም ሁኔታ ነጅሙዲን አዩብና ወንድሙ ሺርኩህ በሙጃሂዱዲን ባህሩዝ ከመንደሯ በተባረሩባት ዕለት ሰላሑዲን ተወለደ። የአንዲትን ሴት ንፅህና በማጉደፍ በሃሰት ስሟን ያጠፋ አንድ የመንደሯ ጠባቂ በሽርኩህ ስለተገደለ ነበር ከመንደሯ የተባረሩት። በህሩዝ የጠባቂውን መገደል እንደሰማ ላባርራቸው ወይስ ልተዋቸው በማለት ለመወሰን ተቸግሮ ነበር። ኋላ ግን የጠባቂው ቤተሰቦች ይበቀሏቸዋል ብሎ ስለፈራ በማባረሩ ቆረጠ። ስጋቱን ገለፀላቸውና በሌሊት መንደሯን ለቀው እንዲሄዱ መከራቸው። ቤተሰቦቻቸውንና አዲሱን ህፃን ዩሱፍ ሳላሑዲንን በመያዝ መንደሯን ለቀው ወደ ሞሱል ተጓዙ።

ኢብን ኸሊካን ‹ዋፊያቱት አል-አዕያን› በተባለው መዕሃፋቸው እንዲህ ብለው ነበር፡- አዩብ በአዲሱ ህፃን ተስፋ ቆርጦ ነበር። መንደሯን ለቀው በሚሄዱበት ጊዜ ህፃኑ አምርሮ ማልቀሱን የገደቢስነት ምልክት አድርጎ ስለወሰደው ሊገድለው ሁሉ ፈልጎ ነበር። "ጌታዬ ህፃኑ ምንም የሚያውቀው ነገር የለምና ይህን ያህል አይማረሩበት። ይህ መለኮታዊ ውሳኔ ነው። ወደፊት የታወቀ ንጉስ ወይም ትልቅ ሰው ሊሆን ይችላል። ማን ያውቃል? ይልቅ ገደቢስ አድርጎ የማየት ስሜትዎን ደብቀው በንክብካቤ ያሳድጉት!" በማለት አንድ ሰው አስጠነቀቀው። እነዚህ ቃላት አዩብ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ ነበራቸው። ወዲያው ስሜቱ አደብ ገዛ። ወደ ሕሊናውን ተመለሰ። ወደ (ኢስላም ጎዳናም ገባ ኢስላምን ተቀበለ)።

አስተዳደግ

አዩብና ሺርኩህ ባግዳድን ለቀው ወደ ሞሱል ሔዱ። በወቅቱ የሞሱል አስተዳዳሪ ከነበረው ዒማዱዲን ዘንኪ ዘንድ አረፉ። የሞቀ አቀባበል አደረገላቸው። ስጦታዎች ሰጣቸው። ምክንያቱም ባህሩዝ የባግዳድ ገዥ በነበረበት ጊዜ ዒማዱዲን ዘንኪ ከሰልጁቶች ጋር ተዋግቶ ነበር። በሠዓቱ አዩብ እና ወንድሙ ከመገደል ወይም የጦር ምርኮኛ ከመሆን አድነውት ነበር። አዩብና ወንድሙ የቲክሪትና የግንቦቹ ተቆጣጣሪ ሁነው ተሹመው እንደነበር መጥቀሳችን ይታወሳል። ዒማዱዲን ዘንኪ በሰልጁቁ መሪ ተሸንፎ ወታደሮቹን በመያዝ በቲክሪት በኩል ለመሸሽ ሲሞክር ከአዩብ እጅ ላይ ወድቆ

ነበር። ያን ጊዜ ነጅመዲን አዩብ ሁለት ነገሮች ይጠበቁበት ነበር መግደል ወይም እስረኛ አድርጎ ማስቀመጥ። ነጅመዲን ግን መልቀቁን መረጠ። ሞሱል እንዲገባ ረዳው። ፍውም የማይረሳ ውለታ ነበር።

ቀደም ብለን እንደገለፅነው ሁለቱ ወንድማማቾች ሞሱል እንደደረሱ የሞቱ አቀባበል ካደረገላቸው በኃላ የሚኖሩበት መሬት ሰጣቸው። በዓማዱዲን ደጋፊነት ቤተሠቡ በደስታ መኖር ጀመረ። ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱን ወንድማማቾች የሠራዊቱ አዛዦች አድርጎ ሾማቸው። ዓማዱዲን በ534 (ሒ.አ) በፅልበክን የያዘ ጊዜ ነጅመዲንን አስተዳዳሪዋ አድርጎ ሾመው ይህ ሹመት ዓማዱዲን በነጅመዲን አዩብ ላይ ምን ያህል መተማመን እንደነበረው ያሳያል።

ሰላሐዲን የልጅነቱን የተወሰነ ጊዜ በፅለበክ ውስጥ አሳለፈ። የሕይወቱን ምርጥ ቀናት በውስጧ ኖረ። ፊደስ ግልቢያ ተማረ። ለጦርነት እና ለጅሃድ ሰለጠነ። የፖለቲካና የአስተዳደር ክህሎቱን አዳበረ።

አባት በኖረበት የአስተሳሰብ መንገድ

ልጅም ይተረጻል ልብ በሉ ሲሄድ

ዓማዱዲንን የተካው ልጁ ኑረዲን በ1154 (እ.ኤ.አ) ደማስቆን ተቆጣጠረ። ሳላሐዲን ወደ ደማስቆ መጣ። ሳላሐዲን ጀግንነቱ እና ጥንካሬው ተሚልተው ያደጉት ደማስቆ ውስጥ ነበር። በደማስቆ ንጉሦች ዘንድ ትልቅ ቦታ እና ክበሬታን አገኘ። በዝምተኛነቱ፣ በትህትናው እና በፈሪሃ አላህነቱ በጣም ይታወት ነበር። በኢስላም እና በሙስሊሞች ጉዳይ ላይም ምንጊዜም የማይበርድ ወኔ ነበረው።

በኑረዲን ጊዜ የደማስቆ ከተማ የፖሊስ ዋና አዛዥ ሆኖ ተሾመ። ደማስቆን ከወንጀለኞችና ከዘራፊዎች በማፅዳትና የከተማዋን ሀኖታና ሠላም በመመለስ በኩል ያደረገው ጥረት ተሳካለት። ህዝቡ በሰላም መኖር ቻለ። አርላህ በሚል ትዕል ስም የሚታወቀው ሐሳን ኢብኑ አመይር የዩሱፍ ሳላሐዲንን ቢሮ እና ስኬት ተቀላቀለ።

አንድ ምክር ሐሰኝ ለሶሪያ ዘራፊ

ተማኝ ወንበዴ አውላቲ ጠላፊ

ከዘመናት ወዲህ ዩሱፍ ተከሰተ

ክህሎት አስተውሎት እጅግ ያካበተ

ያ ነቢዩ ዩሱፍ አቻ ያልነበረው

ውበቱና ለዛው

የተማረ ኩራት ሹማምንት ወይዛዝርት

ሀገር ምድሩ መላው

ይኸኛው ሳተና ፊቱ ማይቆም እቡይ

እየጎማመደ የሰመጠላት ገዳይ

ጅግንነቱን እና ወታደራዊ ልምዱን በማዳበር በኩል ግን ግብዕ ውስጥ ካሳለፈው ጊዜ ጋር የሚስተካከል ሌላ ጊዜ አልነበረም። በ558 (አ.ሒ.) ሻዊር አስ-ሰዕዲ ካይሮን መሠረት ባደረገው የፋጢማይድ ሥርወ መንግስት ኸሊፋ አል-ዓዲል ላይ አመፀ።ኸሊፋው የኑረዲን ማህሙድን እርዳታ በመሻት ወደ ደማስቆ መልዕክት ላከ። ኑረዲን ጥያቄውን ተቀብሎ በአሰዱዲን ሺርኩህ የሚመሩ ወታደሮችን ላከለት። አሰዱዲን የወንድሙን ልጅ ሳላሑዲንን ይዞ ሔደ። በዚህ አጋጣሚ ሰላሑዲን በጦርነት ስልቶች እና ፍልሚያዎች ላይ ወታደራዊ ብቃቱን ማሳየት ቻለ። በ564 (አ.ሒ.አ) በጠላት ላይ ድል ተቀዳጅተው ግብዕን የኑረዲን ማህሙድ ግዛት አካል አደረጓት። ይህ ታሪክ በሚቀጥለው ምዕራፍ በስፋት ይዳስሳል።

ለማጠቃለል ያህል በዕለበክ፣ ደማስቆ እና ግብዕ የሰላሑዲን የልጅነት ሕይወቱና የሁለተኛውና የሦስተኛው አሥርት የወጣትነት ዕድሜው ስብዕና የተቀረፀባቸው ሥፍራዎች ነበሩ። ወታደራዊ ስልጠናዎችን ወሰደ። የህዝቡን ኑሮና ባህል በጥልቀት ተረዳ። በኢስላማዊ ጉዳዮች ላይ የማይበርድ ወኔ ታጠቀ። ራሱን በዕውቀት አበለፀገ። እንዲሁም ከንጉሶች እና ከልዑላን ጋር የነበረውን ግንኙነት በመጠቀም የገንዘብ አቅሙን አደረጀ። እንዲህ እንዲህ እያለ የታሪክን አቅጣጫ መቀየር የቻለ የልዩ እና የምጡቅ ስብዕና ባለቤት ሆነ።